# ፋኖ ተሰማራ በለንደን አንባ!
# አዲዮስ ሠላማዊ ትግል! ቻው፣ ቻው!

ክፍል 3 (ከአያልነሽ)

ለኢትዮጵያ ፍቱን መድኃኒት የሚሆነው ለሠላም ሟች የሆኑ መሀተመ ጋንዲዎችና፣ ያወቁ፣ የበቁ፣ ሊቀ ሊቃውንቶች የሚመሩት ''ዴሞክራሲያዊ የነፃነት ትግል'' እንጅ፣ በአመፅ መንግሥትን ለመገልበጥና በመሣሪያ ትግል ሱስ ያበዱ ፀረ-ሠላም ''ቼ ጉቬራዎች'' በሚመኙት ቅዠት የኢትዮጵያ ሥርዬት አይመጣም። ዛሬ የ''ኢሕአዴግዋ'' ኢትዮጵያ የምትፈልገው ''ሠላምንና የሠላምን ልማት ነው'' እንጂ ''የጠመንጃ ነካሾችን'' እንቢልታና ጡሩንባ አይደለም አሉ። ያኔ በ ''ደህናው'' ጊዜ ወያኔ/ኢሕአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ ሰሞን ከአሜሪካ የገቡት ምሁር። ማን?



(የፎቶ ምንጭ ኢትዮ ላየን)

አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ደግሞ ከ30 ዓመት በኋላ ለሦስት አሥርት ዓመታት ያህል ዕድሜህን ያሳጥረው የሚል ዕርግማንና መዓት ሲያወርዱበት፣ የ''ፋኖ ተሰማራ'' ሱሰኞች እያሉ በ''ሱሰኞች'' ላይ ሲሳለቁ የኖሩትን ያህል፣ ይኸውና ዛሬ የትጥቅ ትግል ጥሪ በቅርቡ በአሰሙበት ሰሞን፣ ይሄንን የመረጡትን የስልት አማራጭ ሲያውጁም በግላቸው እንደሆነም አጫውተውን ነበር። እንዲያውም አሉ አቶ አንዳርጋቸው፤ እንዲያዉም እስካሁን ድረስ ቅንጅት ለምን ዝም እንዳለና እንዳላሳናበተም አላውቅም ብለው በለሆሳስ ነበር ድክምክም ባለ ድምፅ ይሄንን ቃል የተናገሩት። ንግግራቸው እኔ እንደገባኝ ከሆነ እነአቶ አንዳርጋቸውን የብርቱካን ሚደቅሳው ቅንጅት ለምን እስካሁን ዝም እንዳላችውና አቶ አንዳርጋቸውንም ያስገረማቸው ጉዳይ እንደሆነ ነው የተረዳሁት። አደራ! ግንዛቤዬ በትክክል ካልሆነና በትክክል ካልተረዳሁትም አቶ አንዳርጋቸው ቢያርሙኝ፣ ቢያስተካክሉኝ ፈቃዴ ነው። የሆኖ ሆኖ ግን እውነትም (የብርቱካን ሚደቅሳው) ቅንጅት ዝም ማለቱ እኔም አሁን ሳስበው ከዘመናዊነት ወይስ ከፈራነት ይሆን? እንድል አስገድዶኛል። የሆነ ይሁን እንጅ መቼም በዚህ ላይ አስተያየት የለኝም፤ እንዳትቀየሙኝ። አንድ ነገር ግን ትዝ አለኝ። ድሮ ድሮ ልጆች ሆነን ጓደኛሞች የሆንን ልጆች ስንጨዋወት፣ በእኛ መሐል (በጓደኛሞች መካከል) ጨዋታችንን ሌሎች እንዳይሰሙብን ለማድረግ ስንፈልግ፣ የወፍ ቋንቋ የሚሉትን እንጠቀም ነበር። በኔ ዘመን የነበራችሁ ልጆች ይህንን ታስታውሱ ይሆናል፤ ትዝ አይላችሁም? አሁንም አቶ አንዳርጋቸውና ወይዘሪት/ወይዘሮ ብርቱካን ሚደቅሳ የሚነጋገሩበት ንግግር በወፍ ቋንቋ መሰለኝ፤ ልክ ላልሆን እችላለሁ፤ ግን መሰለኝ ነው

ያልኩት። ከዚህ የወፍ ቋንቋ በኋላ እነ አቶ አንደርጋቸውም ወዲያውኑ ከቅንጅት የመልቀቃቸውን ዜና በመግለጫ አስደግፈው ከ5 የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር መገለላቸውን ያስቀመጡበትን መግለጫ አስነበቡን ወይ ጉድ። እነኝህ 5 የላዕላይ ምክር ቤት አባል ነበርን የሚሉ ሰዎች አሁንም ለእነ ብርቱካን ሚደቅሳ መልዕክታቸውን የወፍ ቋንቋ ባልኩት ሲያስተላልፉ፣ ሲሆን ሲሆን እስካሁን ዝም ማለታችሁ ደግ አልነበረም፤ አሁንም ቢሆን ግን እኛ ከድርጅቱ ለቀናል የሚል መግለጫ አውጥተን በትነናልና አልዘገዬም፤ ስለዚህ ተረጋጉ የማለት ያህል ነው አባባሉ። ነገሩ ይኸው ነውና መንገዱ ለእኛም ሆነ ለእናንተ የማያስቸግር፣ ወደፊትም ላሰብነው የጋራ ዓላማችንም የሚቀል አካሄድ ነው ብለንም እገምታለን። በተጨማሪ እናንተም እንደልባችሁ፣ እኛም እንደልባችን ለመሆንና ለመናገር፡ ለጠላቶቻችን ማደናገሪያ፣ ለተከታዮቻችንም ማዝገሚያ ይሆን ዘንድ፣ የሚል ዓይነት የወፍ ቋንቋ ነው የንግግራቸው ዚቅ። እኔ መቼም እርግጠኛ ነኝ። ወያኔ ለሁለቱም ክፍሎች ለሰላሳ ወዳጂ ነው፤ ትንሽ ከመንገዱ የወጡና ያስቀጡት ከመሰለው ደግሞ እንዴ! እንዴት ነው ነገሩ እየተስተዋለ! ብሎ ታገሱ የማለት ያህል ሹክ ይላቸዋል።

ወይ አጋጣሚ! አቶ አንዳርጋቸው ይሄን ባሉ በቀናቶች ውስጥ ደግሞ በአሜሪካ አገር አንድ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ "የፍትህና የዴሞክራሲ ትግል" አቅጣጫ ምን መሆን እንደሚገባው፣ "በነፃ እየከፈላችው" በአሜሪካ ተራራ ላይ ተቀምጠው ጥናት ላይ የባጁት ዶ/ር ብርሃኑም፣ ጥናታቸውን ጨርሰው ነው መሰል ከአቶ አንዳርጋቸው አቋም ጋር የተስማማና አብረውም የሚዘልቁበትን አቋማቸውን ይፋ አድርገዋል። ለተወሰነ ጊዜ የትግሉ አቅጣጫ ጠፍቷቸው በጨለምተኝነት ሲናውዙና ሲጨነቁ የነበሩት ዶክተር፣ ሲገለጥላቸው ደግሞ ወዲያውኑ ደረሰኩ፤ ከጠፋሁበት ጨለማም ወጣሁ የሚል የአቋም መግለጫ ነው ያወጡት። ይህ መግለጫ በድርጅት ስም ይሁን በሌላ፣ እስካሁን ይፋ አልሆነም። ብቻ ከብርቱካን ሚደቅሳው ቅንጅት እንደተለዩ ነው የሚያወሳው የመግለጫው ይዘት። ምናልባት ዶክተሩ ለአዲስ አበባ "ከንቲባ" ታሰበው የነበሩ ስለሆኑ ሌላ ዝባዝንኬ አያስፈልገም፣ ለዚህ መግለጫ ይሄ ታዋቂነታቸው ብቻ ይበቃዋል ከሚልም ይሆናል። የኔ ነገር! ጨዋታ አበላሸሁ መሰለኝ "ለንጉሡ ያጎንብሱ" መባሉን ዘንጌቼ። ሃ! ሃ ! ሃ ! ሃ ! ጊዜው እኮ ረዘመና ነው ። ይቅርታ "ክቡር" ከንቲባ! አለማወቄ ከክፋት እንዳይታይብኝ። መግለጫው ግን በአንዳንድ ድረ ገጾች ላይ መለጠፉን ተመልክቻለሁ። እንዲህ ይላል "እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከቅንጅት መልቀቃቸውን አሳወቁ"። ሰረዝ የኔ።

እሺ! ወደ ቁም ነገሩ እንመለስ። አሁን እንግዲህ የትጥቅ ትግሉ ታውጇል። ጦሩም በዝግጅት ላይ እንዳለና በቅርቡ በጣም ቅርብ በሆነ ጊዜ ደግሞ ተዓምር እንደሚያሳይ፣ አቶ አንዳርጋቸውም እያስጠነቀቁ ነው። ግን ስለ ጦሩ የእንቅስቃሴ ሁኔታና ዝግጅት፣ በሳቸው ፓልቶክ ላይ እንደሚነገረውና እሳቸውም እየቀረቡ እንደሚያስረዱት፣ ዜናውም

ከሚተላለፍበት ቀጠና (ከእንግሊዝ ሳይሆን አይቀርም) አንፃር ብንመለከተው፣ የጦሩ አደረጃጀት ለእኔ የጎሬላ እንቅስቃሴ ዓይነት አልመሰል ብሎኛል፤ የሌላውን አላውቅም። እንደ አሜሪካው የኢራቅ ወረራ ዓይነት በመደበኛ ጦር የተደራጀ ይመስላል። የሚጀምረውም በጎሬላ ዋር ፌር ሳይሆን በመደበኛ ወታደር መሰለኝ። ለማንኛውም የበለጠ ለማብራራትና ለመወያየት ደግሞ በሜይ 11 ላይ ቀጠሮ ተይዟል ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር። አቶ አንዳርጋቸው ልክ ነኝ? ካልሆንኩም ለአጭር ጊዜ ብቅ ብለው ያብራሩልናል፤ ምን ችግር አለው። ግሩም! በቅርቡ ተዓምር ስለሚሰራው ስለዚህ ሠራዊት እንቅስቃሴ ሲወራ ምንን አስታወስኩ መሰላችሁ የሳዳሙ የኢራቅ ኢንፎርሜሽን ሚኒስትር መሐመድ ሰዒድ አልሻሃፍ ትዝ አሉኝ። አንበሳ ነበሩ በፕሮፓጋንዳው ረገድ! እኔ ልሙት ። ምን ማድረግ ይቻላል ታዲያ! የአሜሪካው ጦር ሲገባ የሳቸውም ድምፅ አብሮ ጠፋ። አቤት! አቤት! አቤት! በፕሮፓጋንዳው እስከ ደም ጠብታ እንደሚባለው ዓይነት ነበሩ። ጉድ እኮ ነው።

የተከበራችሁ አንባቢዎች!
ትዝ ይላችሁ እንደሆነ በክፍል 2 ፅሁፌ ላይ በጥያቄ መልክ ያስቀምጥኳቸው አንዳንድ ነጥቦች ነበሩ። ለምሳሌ የትጥቅ ትግሉ መቼ እንደሚጀመር? የጦሩ አዛዥ (ኮማንደር) ማን እንደሆነ? የዕዝ ማዕከሉ የት እንደሆነ? ጦሩ ተጠሪነቱ ለማን እንደሆነ? ወዘቴ... ጠይቄ ነበር። ሌላም ሌላም። እንዲሁም የትጥቅ ትግሉ ግብ/ዓላማ? የሚያነጣጥረው ማን ላይ ወይም ዒላማ ያደረገውስ ማንን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን። ለእኔ ጥያቄዎቼ አሁንም መሠረታዊ ናቸው። በጣም ቀላሉን ነገር አንስቼ የጥያቄዎቼን ክብደትና ይዘት ላስረዳ። አዛዥ (ኮማንደር) የሌለው ወታደር ሊኖር አይችልም። ሊያነጣጥርበት የሚችል፣ ዒላማ የሌለው ወታደር በባዶ ሜዳ ዓይኑን እያጨለቀ ሊተኩስ አይሞክርም። ለመተኮስና ለማነጣጠር ከፈለገ ደግሞ ሊተኩስበት ወይም ሊያነጣጥርበት ያሰበዉን ቦታ/ዒላማውን አስቀድሞ ቢያንስ በአሸዋ ገበታ ስሎ ለሚያዘው ጦር ማሳየት/ማስጨበጥ አለበት። ለነገሩ ከላይ የጠቀስኳቸውን ጥቂት ነገሮች ቀላል የሚመስሉ ግን ወሳኝ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮች አንድ አዛዥ (ኮማንደር) በሥሩ ላሉት ወታደሮች ሥዕላዊ መግለጫ ሊሰጠው ወይም እንዲሰጠው ወታደራዊ ሳይንሱ ያስገድደዋል። ምን ማለት ነው? ከላይ የጠቀስኳቸውን ጥቂት ነገሮች ወደ ተግባር ለመለወጥና ሥራ ላይ ለማዋል የሚነሳ ኃይል መጀመሪያውኑ ሲያስብ ይህ ጦር የሚያነጣጥርበት ወይም የሚተኩስበት ዒላማ ማንና ምን ላይ እንደሆነ ከመተኮሱ በፊት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት ማለት ነው። በክፍል 2 ጽሁፌ ላይ ከአቀረብኩት ዋናውና መሰረታዊው ጥያቄ ደግሞ ይሄ ጦር የሚተኩስበት/የሚያነጣጥርበት ጠላት ማን ነው? የሚል ነበር። ይሄንን ወይም መሰል ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ሾላ በድፍን እንደሚባለው "ፌዝ" ወይም "አሉባልታ" እያሉ ማለፉ ቀላሉ ዘዴ ሆኖ ተገኝቷል። ጥያቄው ግን መሠረታዊ ነው። ይሄ በትንሹ ወታደራዊው ሳይንሱ የሚጠይቀው ቲዎሪ (ንድፈ ኃሳብ) ነው። ለመጀመር አሸዋ ገበታ ሰርቶ ማሳየትን ከጠየቀ፣ ሲገቡበት ደግሞ

ኡምምምምምምም ብዬ ልለፈው። ለዚህ ነው ለሚነሱ ጥያቄዎች ሆኑ ለሚሰጡ ኃሳቦች ግልጹንና መሬት ላይ የሚታየውን ነገር በተጨባጭ ለማስረዳት፣ ለማብራራት ባልተቻለበት ሁኔታ ነገሮችን ለተጨባጭና ለውጤት ማብቃትና ማድረስ፣ ዲስኩር እንደ መስጠት ወይ እንደመናገር አይቀልም የሚባለው። በሌላ አነጋገር ”ለተቀመጭ ሰማይ ቅርቡ” እንደሚሉት መሆኑ ነው። ቁም ነገሩ ጥያቄዎች፣ ትችቶች መልስ አገኙ አላገኙ፣ ታዛቢ የሚባል ነገር ደግሞ አለ፤ ምንጊዜም የሚኖር። ይህ ታዛቢ የሚባለውስ ምን ይላል? ሰሞኑን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ”የሞራል እኩልነት ጥያቄዎችና የአመለካከት ችግራቸው” ባሉት ባለ 16 ገፅ ጽሁፋቸው፣ ለዚህ ጽሁፋቸው መነሻ የሆናቸዉንና ያስደነገጣቸውን ነገር ዋቢ አድርገው አስፍረዋል። እስቲ ይህ ያስደነገጣቸው አባባል ምን ይሆን? ከፅሁፋቸው ልጥቀስ፥

> ”ባለፋት ሁለት ሳምንታት ለጉዳይ ወደ ደቡብ አፍሪካ በሄድኩ ጊዜ አንድ ከኢትዮጵያ ለህክምና የመጣ ወዳጇን አግኝቼ ትንሽ ገብስ ገብሱን ከተጨዋወትን በኋላ ቀስ በቀስ ወደማይቀረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወሬ ገባንና ብዙም ሳንቆይ አንድ በጣም ጠንካራ የሆነና በጊዜው ትንሽ ያስደነገጠኝን ነገር ተናገረ። ሰውዬው ያለው ”መለስ ዜናዊ መሐመድ አላሙዲና እናንተ ሁላችሁም አንድ ናችሁ። ሁላችሁም ራሳችሁ የምትፈልጉትን ነገር በሕዝብ ላይ ለመጫን ነው የምትፈልጉት። ለሕዝብ ፍላጎት ደንታ የላችሁም።” ይላል።

ይሄ አባባል ከታዛቢ፣ ያውም ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ወዳጇ ካሉት ሰው የተሰነዘረ እንደሆነ ነው ዶክተሩ በጹሁፋቸው ላይ የጠቀሙት፤ ያውም ከጠላት ሳይሆን ከወገን ወይም ከወዳጇ ሠፈር የተሠነዘረ። አባባሉም እንዲያው ዝም ብሎ ከሰማይ የወረደም ነው ሊባል አይችልም። ግለሰቡ ካዩት፣ ከሰሙት፣ በተጨባጭ ደግሞ ከሚኖሩት ሕይወት ጋርም የተያያዘ ለመሆኑ የትችቱ ይዘት ገላጭ ነውና ማስረጃ አይጠይቅም። ከቅድመ ምርጫ 97ና ከድህረ ምርጫ 97 በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረውን እያየነው፣ እየሰማነውና እየተከታተልን ነው። የሰዉዬው ትችት (ንዴትም ተጨምሮበት ከሆነ) የንዴቱ ምንጭ የሚያስገርም ሊሆን አይገባም። ይልቁንም ትችቱን በቅንነት ለሚመመለከተው የሰዉዬው ኃሳብ ከአንድ ተራ የኔቢጤ ወይም ቅንና የተገፋ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ፣ የተሠነዘረ ትችት አድርገን ከወሰደነው አስተማሪነቱና መልዕክቱ ቀላል አይደለም። ሁለት ነገሮችን ያመላክታል፣ የሰውዬው ትችት። ሀ) ሕዝባችን አሁን ያለበትን የመከራ ሮሮ፣ ለ) ከዚህስ በኋላ የሚቀጥለውና ስለሚጠብቀው ተስፋውና ምኞቱንም ገላጭ ነው። ሕዝባችን ደግሞ እያንዳንዳችንን እንዴት እንደሚመለከት ከማስተማሩ ሌላ፣ የሰውዬው ትችት እያንዳንዳችን ራሳችንን እንድንፈትሽ ከወዳጅ እንደተሰጠ ምክር ተደርጎ ነው መወሰድ ያለበት እላለሁ።

እየረሳን ወይ እያረሳሳን ካልሆነ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፀረ ወያኔው ትግል ተጋድሎ ከማንም በላይ መስዋዕትነት እስከመከፈል ሁሉ ሄዶ የተሰረቀ ድምፁን ለማስመለስ ያደረገውንና እስከመጨረሻው ጫፍ ሊያደርስ ያሰበውን ትግል፣ ከመረጠው ወገኑ በቴሌቭዥን እንዲያቆም ሲጠየቅ፣ ይህ ግፍን ተሸክሞ የሚገኝ ህዝብ በምንም ዓይነት መንገድ ስሜቱን ሊገልጽ ቢሞክር ከሞራል አንጻር አግባብነት ያለውና ሲያንሰው ነው ባይ ነኝ። ይልቁንስ የተሰጠውን ትችት በደንብ መመርመርና መፈተሸ (በበጎ ለሚመለከተው) ጠቃሚነቱ አንድና ሁለት አይባልም። እንዲህ እንዲህ ዓይነት ትችቶች ከየትኛውም አቅጣጫ ቢመጣ በነገሮቹ ይዘት ላይ አትኩሮ፣ ሰክኖ፣ ጊዜ ወስዶና ረግቶ ለመመልከትና ራስን ለመፈተሽ የሚረዳ ከወዳጅ እንደተሰጠ ምክር/ክኒን ተደርጎ ነው መታየት/መወሰድ ያለበት የምለው።

ዶክተር ብርሃኑ! ''ምክር የት ትገኛለሽ ቢሏት ከደጃ'' አለች ይባላል። ማረምና ማረቅ የሚገቡ ስህተቶችን በተደጋጋሚ በመሥራት፣ ያ የተሠራ ስህተት ደግሞ አንዴ ካለማውቅ፣ ሊባል ይችላል፣ ሁለተኛ ሲደገም ደግሞ በመርሳት ወይ በመቸኮል ተብሎ ሊታለፍ ይችላል። ሦስተኛና አራተኛ ሆኖ ከቀጠለና እንደ ግብ ተቆጥሮ ''ማንም ምንም ቢል'' ጉዳዬ አይደለም፣ ''ያሉባልተኞች ወሬ'' ነው እያሉ መቀጠልን እንደ ጀብድ ከታዬ ዶ/ር ብርሃኑ ወዳጄ ያሏቸው ግለሰብ/ሰው የሰጡት ትችት ቦታውን አግኝቷል ማለት ነው። ስለዚህ ችግሩ ያለዉ ከተቼት ሰውዬ ጋ ሳይሆን ከተተቼት ''ሊቆች'' ዘንድ ሳይሆን ይቀራል ትላላችሁ? ከላይ የተጠቀሰውን አባባል ሰውዬው ለምን እንደተጠቀሙ እንዲብራራ ዶ/ር ብርሃኑ ደግመው ሲጠይቁ፣ ሰውዬው የመለሱላቸውን ከዚሁ ከዶ/ር ብርሃኑ ፅሑፍ ወስጄ ልጥቀስ፥

> ''መለስ የሚፈልገውን ለማግኘት (ሥልጣን ላይ ለመቆየት) ይገላል፣ ያስራል፣ ይዋሻል፣ የሕዝብ ንብረት እንደ ግል ኪሱ ይጠቀማል። አላሙዲን የሚፈልገውን ለማግኘት (ገንዘብ ማካበት፣ በገንዘብ የሚገኝ ተሰሚነት…ወዘተ) ገንዘቡን ይጠቀማል። ከሞላ ጎደል ይጠቅሙኛል ያላቸውን ሰዎችም ይገዛል። እናንተም ቃላትን ተጠቅማችሁ የምትፈልጉትን ነገር በህዝቡ ላይ ለመጫን ትሞክራላችሁ። ጉልበት አትጠቀሙ ይሆናል፣ ገንዘብ የላችሁ ይሆናል፣ ግን ህዝቡ የሚፈልገውን ከማድረግ ይልቅ እናንተ የምታምኑበትን ነገር በህዝቡ ላይ ለመጫን ነው የምትፈልጉት'' ነበር ሰውዬው ያላቸው።

ታዲያ ይሄ አባባል ስህተቱ ምን ላይ ነው ዶ/ር ብርሃኑ? ዛሬስ በአደባባይ እየታየ ያለው ይኸው የቃላት ጦርነትና የቃላት ጨዋታ አይደለም እንዴ? ይሄ እንግዲህ አሁንም ካልገባን፣ ችግሩ ያለው ከተችዎች ሳይሆን ''ብንሆንስ ምን ይጠበስ'' ከሚሉ ግብዞች ደጅ አካባቢ የሚገኝ ይመስለኛል። ከሆነ ለግብዞች ደግሞ ሰውዬው የሰጡት

ትችትና አገላለጽ እንከን የለሽ የሚባል ነው። ለሁሉም አቶ አንዳርጋቸው! እንበርታ እስቲ።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሰሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ቸር ይግጠመን
ሚያዚያ 24 ቀን 2000 ዓም(ሜይ 1/2008)